17ኛ ዓመት ቁጥር 90 አሶሳ
የካቲት

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት
ልሣነ- ሕግ ጋዜጣ
የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል መንግስትም/ቤት ጠባቂነት የወጣ

## አዋጅ ቁጥር 90/ 2002 ዓ.ም.

## የተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ምክር ቤት አባላት ሥነ ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣውን አዋጅ እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ፣

### መግቢያ

የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት ተሻሽሎ በወጣው የክልሉ ህገ መንግሥት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በህዝቡ የተጣለበት ኃላፊነት በአግባቡ መወጣት ስላለበት፣

በምክር ቤቱ ዴሞክራሲያዊ የአሠራር ባህል የሚዳብርበት ከአገሪቱ ህጐች ከአለም አቀፍ የፓርላማ መርሆች፣ አሠራሮች እንዲሁም ልምዶች ጋር የተጣጠመ አዋጅ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በተሻሻለው የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት ህገ መንግሥት አንቀጽ 49 (3) (3.1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### አንቀጽ 1 አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ምክር ቤት የአባላት ሥነ ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራርን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 90/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### አንቀጽ 2 ማሻሻያ

የተሻሻለው የክልሉ ምክር ቤት የአባላት ሥነ ምግባር፣ የህግ አወጣጥ ሥነ ሥርዓት፣ የኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሠራርን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 65/1999 አንቀጽ 5 እንደሚከተለው ተሻሽሏል።

የምክር ቤቱ የመክፈቻ ስብሰባ፣ የአፈ ጉባኤና የምክትል አፈ ጉባኤ አመራረጥ፣

ሀ/ በተሻሻለው የክልሉ ህገ መንግሥት አንቀጽ 61(3)ተ መሠረት የመጀመሪያ የምክር ቤቱ መሥራች ጉባኤ በክልሉ ፕሬዚዳንት አማካኝነት ጥሪ ይደረጋል፣

ለ/ ጠቅላላ ምርጫ ከተካሄደ በኋላ የሚመሠረተው የአዲሱ ምክር ቤት

የመጀመሪያ ስብሰባ በቀድሞው ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ወይም በምክትል አፈ ጉባኤ ጥሪ ይደረጋል፡፡

ሐ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ይህንን አዋጅ ተከትሎ በሚወጣው ደንብ መሠረት አፈ ጉባኤውንና ምክትል አፈ ጉባኤውን ያስመርጣል፡፡

መ/ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት ተመራጩ አፈ ጉባኤ ከቀድሞው አፈ ጉባኤ የሥልጣን ርክክብ እንዲያደርጉ በማድረግ መድረኩን ለአዲሱ አፈ ጉባኤ ያስረክባል፡፡

**አንቀጽ 3 አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በክልሉ ልሣነ ህግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አሶሳ**

**መጋቢት -ቀን 2002 ዓ.ም.**

**አህመድ ናስር አህመድ**

**የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግሥት**

**ኘሬዚዳንት**